በህዝቦች መካከል ሊኖር የሚገባውን መቀራረብ እያደፈረሰውና የህዝቡንም የሀገሩና የአካባቢው ባለቤትነት መንፈስ እያደከመው መሆኑ የስጋት ምንጭ በመሆኑ፣

4 ለዘመናት ሳይፈታ የኖረው የብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጥያቄ ዛሬም በኢህአዴግ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ባህሪ፣የተሳሳተ ፖሊሲና አሰራር ምክንያት መፍትሔ ሳያገኝ መቅረቱና ጥያቄው ወደ የባሰ ውስብስብ ችግር ውስጥ ሀገራችንን እንዳይከታት ወሳኝ የእርምት እርምጃዎች በአስቸኳይ መወሰድ እንዳለባቸው በማመን፣

5 የኢትዮጵያ መሰረታዊ ችግሮች፣ ሁሉንም ባለድርሻዎች (ማለትም የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሲቪክ ማህበራት የሙያ ማህበራት ወዘተ) ባሳተፈ መልኩ እንዲፈቱ በስልጣን ላይ ያለው የኢህአዴግ መንግስት በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ገንቢ ምላሽ ባለመገኘቱ ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ መሄዳቸው በእጅጉ ስላሳሰበን፣

6 በአብዛኛው የሀገራችን ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎች በሚኖሩ ሕዝቦቻችን መሃከል ከዚህ ቀደም ያልተለመዱ ግጭቶች እየተከሰቱ፣ በሰው ሕይወትና ንብረት ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ መሆኑ በእጅጉ ያሳሰበን ሲሆን፣ ለዚህ አሳዛኝ ክስተት የኢሕአዴግ መንግስት መፍትሔ ለመስጠት ያለሙብቃቱ በእጅጉ ስላሳሰበን፣

7 የኢህአዴግ መንግስት የኢትዮጵያን ዳር ድንበርና ሉዓላዊነት የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ ሊወጣ ያለመቻሉ በእጅጉ ስላሳሰበን፣

8 በሀገራችን አስከፊ ረሃብ፣ የኑሮ ውድነት፣ ሥራ አጥነትና ያፈጠጠ ድህነት ከስርዓቱ በሙስና ውስጥ መዘፈቅ ጋር ተደማምረው የሕዝቦቻችንን ህልውና በእጅጉ እየተፈታተኑት መገኘታቸው ስላሳሰበን፣

9 የሀገራችንን መሰረታዊ ችግሮች በሰላማዊ የፖለቲካ ውድድር አሸንፈው በሚወጡ አማራጮች ለመፍታትና የመቻቻል ፖለቲካዊ ባህልን ለማዳበር የሚያስችልና የዴሞክራሲ ስርዓትን እውን ለማድረግ የትግል ትብብር መፍጠር የወቅቱ የኢትዮጵያ ህዝብ አንገብጋቢ ጥያቄ መሆኑን በማጤን፣

10 እስካሁን ድረስ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ቢያንስ በመለስተኛ ፕሮግራም ዙሪያ በመሰባሰብ የኢትዮጵያን ህዝብ አስተባብረው በሰላማዊ መንገድ የሚደረገውን ትግል በተጠናከረ ሁኔታ በመቀጠል፣ በፖለቲካው ውድድር አሸንፎ የሚወጣ አማራጭ ሆነው በመቅረብ፣ ለመንቀሳቀስ ያለመቻላቸውን ድክመት በመገንዘብ፣

ይህንን ‹‹መድረክ ለዲሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ ›› በመባል የሚታወቅ የምክክርና የውይይት መድረክ፣ ከዚህ በታች በተመለከቱት መርሆች ላይ በመመስረት አብረን ለመስራት ተስማምተናል። መድረኩም መርሆቹን ለሚቀበሉና



http://www.EthiopiaZare.com

ለሚያሟሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች ሁሉ በአባላቱ ሙሉ ስምምነት ክፍት ይሆናል።

## 11 የመድረኩ የጋራ መርሆች

ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩባትና ማህበረ - ኢኮኖሚያዊ ፍትህ የሰፈነባት፣ በብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት ላይ የተመሰረተች፣ የበለፀገች ኢትዮጵያን መገንባት። ለዚህም፣

11.1 ሰብዓዊ መብት በሁለተናዊ መልኩ መከበር፤

11.2 ነፃና ገለልተኛ የፍትሕ ስርዓት ተዘርግቶ የሕግ የበላይነት በተግባር መገለጽ፤

11.3 ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለ ገደብ መከበር፤ማለትም:-

ሀ. በነፃ የመደራጀትና የመንቀሳቀስ ያልተገደበ መብት፤

ለ. የመናገር፣ የመፃፍና፣ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት፤

ሐ. ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ በገለልተኛ ምርጫ አስፈፃሚዎች በተአማኒነት መከናወን፤ እና

መ. መድበለ -ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ፤

እውን የሚሆኑበትን ስርዓት መገንባት።

11.4 የግለሰብ፣ የብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦችና የቡድን መብቶች በተጓዳኝነት መከበር፤

11.5 ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት መቆም።

## 12. የመድረኩ የጋራ ግቦች

12.1. በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ በሚንሸራሸሩ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ በጋራ የምንስማማባቸውን አቋሞች አንጥሮ ለማውጣት እንዲያስችል የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት፣

12.2. በሀገራችን ነፃና ፍትሀዊ ምርጫ እንዲካሄድ ገዢው ፓርቲና መንግስት አመቺ ፖለቲካዊ ምህዳር እንዲፈጥሩ የተባበረ ትግል ማድረግና ለሚቀጥለው የ2002 ዓ.ም ሀገራዊና ክልላዊ ምርጫዎች የጋራ ስልት መንደፍ፣

12.3. ገዢው ፓርቲ ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ወሳኝ በሆኑት በተቃዋሚ ድርጅቶች፣ በአባሎቻቸውና ደጋፊዎቻቸው፣ በሲቪል ማህበረሰቡና ግለሰቦች፤ እንዲሁም በነፃው ፕሬስ ላይ የሚያደርሰውን ጫና በህጉ አግባብ በጋራ መከላከል፣

12.4. ለወቅታዊ ህዝባዊና ሀገራዊ ጥያቄዎች መፍትሄ ለመሻት፣ የጋራ መግለጫዎችን ማውጣትና ለጥያቄው ህዝባዊ የድጋፍ እርምጃዎች በሰላማዊ-ህጋዊ አግባብ ማደራጀት፣



http://www.EthiopiaZare.com

12.5 ከላይ የተጠቀሱትን ግቦች ለማሳካት ለሚካሄደው ትግል አለም አቀፍ ድጋፍ ለመሻት የተባበረና የተጠናከረ የጋራ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ማካሄድ::

ስለሆነም፣ ይህ በኢትዮጵያ ተንሰራፍቶ ያለውን ፈርጀ ብዙ ችግሮች ለማስወገድና ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ዙሪያም ያለውን ተባብሮ ለመስራት የያለመቻል ድክመት ለመቅረፍ የተወጠነው መልካም ጅምር የመላውን ህዝባችንን ድጋፍ እንዲያገኝ ጥሪ እናደርጋለን::

- የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
- ኦሮሞ ፌደራሊስት ዴሞክራዊያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን)
- የሶማሌ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት (ሶዴኃቅ)
- ዓረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉዓላዊነት (ዓረና)

ሰኔ 17 ቀን 2000 ዓ.ም

አዲስ አበባ

http://www.EthiopiaZare.com